# መግቢያ

## የክርስቲያን አምልኮ ልምምድ

### የአምልኮ ዓላማና ትርጉም

ክርስቲያኖች በየሳምንቱ ለአምልኮ በጎጆ ቤት ፣በልዩ ቅርፅ በተሰሩ ካቴድራሎች ፣በእሥር ቤቶችና በአረጋዉያን ማጦሪያ ማዕከል፣በሕንጻዎች ዉስጥና በማንደር አደባባዮች፣ እንደዚሁም ልቅ ተደርገዉ በተሰሩ በትላልቅ የአምልኮ አዳራሾች እና በገጠራማዉ አካባቢ በሚገኑ የአምልኮ ማጠሊያዎች ሳይቀር ይሰበሰባሉ፡፡በእንደዚህ ዓይነት በተለያየ አወድ የሚከሄድ አምልኮ ይዘቱም እንደዛዉ ልዩ ልዩ እንደሚሆን አይካደም፡፡አንዳንድ ማህበረ ምእመናን በጥንቃቄ ተጠንቶ የተዘጋጀ ስብከት ያደምጣሉ፤ሌሎች ደግሞ ያለምንም ዝግጅት በስሜት የታጀበ ስብከት ይሰበካሉ፤አንዳንድ አጥቢያዎች በሮክ ባንድ በሚስለ ሙዚቃ ታጅበዉ ይዘምራሉ፣አንዳንዶች ደግሞ በጥንታዊ ትላልቅ ፒያኖዎች ይታጀባሉ፣ሌሎች ከባንድ ጋር በማሆን በአስመላኪዎች ይታጀባሉ፣አንዳንዶች ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ይጠቀማሉ፣ሌሎች ደግሞ ምንም አጃቢ ሳይኖራቸዉ ያመልካሉ፡፡አለባበስንም በተመለከተ አንዳንዶች ለእሁድ አምልኮ ተገቢ የሚሉትን አለባበስ ለብሰዉ ያመልካሉ፤ሌሎች ደግሞ ባህርዳር ለሽርሽር እንደሚሄድ ሰዉ ግድ የለሽ አለባበስ ለብሰዉ ለማምለክ ይመጣሉ፡፡

ይሁን እንጂ የተለያየ ባህላዊ አገላለጾችና የአምልኮ ዓይነቶች ቢኖሩም ቅሉ ደግሞ ከባህል በላይ ለክርስቶስ ወንጌል ደግሞ ታማኝነትን የሚያስጠብቁ በዛ ያሉ ሁሉንም ዓይነት የክርስቲያን አምልኮ የሚመለከቱ ደንቦች አሉ፡፡በተለይም ትዉልዱ በሚያቋርጥ በልዩ ልዩ የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ ትኩረት በሚያደርግበት በዚህ ዘመን፤ሚዎች እንዲለሙድ ሊተጉበት የሚገባ ዋና ነገር ቢኖር ከባህል ያለፈ፣ መደበኛ የሆነ የክርስቲያን አምልኮ ማስፈርት የሚያሟና በንቃት በታማኝነት አምልኮን የሚለማመድ ማህበር መፍጠር ሊሆን ይገባል፡፡ለእነዚህ መሠረታዊ የአምልኮ መሥፈርቶች ትኩረት ያለማስጠት፣ለእዉነተኛ የቃሉ አገልገሎት አለመትጋት፣መሰረታዊ የሙዚቃ ስልት ያለማጠቀም እና ትክክለኛ የአምልኮ ሥርዓት ያለመቅረፅ ለክርስቲያን ሕይወት ተስፋ ከሆነዉ የክርሰቶስ ወንጌል ፈቀቅ ሊያደረግና ማስናከል ሊሆን ይችላል፡፡ ባህል ዘለል የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ትላልቅ መጻሐፍት ማፃፍ ይቻል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጽሁፍ የተጠቀሱት አጭር ሚዳቶች ደግሞ ለሁሉም ዓይነት የክርስቲያን አምልኮ መድረኮች በሚመለከት በበቂ ሁኔታ ጭብጥ ሊሰጡ የሚችሉ ሁነኛ ሀሳቦች ናቸዉ፡፡

**1. የክርስቲያን አምልኮ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ* ሊሆን ይገባል፡፡**

መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔርና ክርስቶስ ስለዋጃት ዓለም ሚዳት እንዲኖረን ዋና የእዉቀት ምንጭ ነዉ፤ስለዚህ አምልኮ ሁነኛ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ሊታጀብ ይገባል፡፡እንደዚሁም የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ባሕሪዉንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮት ማክተትና መሳል ይጠበቅበታል፡፡በአምልኮ ላይ የሚገለጡ ልምምዶችን በተመለከተም ደግሞ በግልፅ ለተቀመጡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዞች የሚገዛና ስለተሳሳተ አምልኮትም በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ለተገለጡት ግልፅ ማስጠንቀቂያዎች ቸላ የማይል ወይም ትኩረት የማይነፍግ ሊሆን ይገባል፡፡አምልኮ በዋነኛነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚናገረዉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ፣በፍጥረት ሁሉ ላይ አዳኝነቱን ሊገለጥ ስላለዉ የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በመግለጥ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡

**2. የክርስቲያን አምልኮ እግዚአብሔርም ሰዉም የሚገናኙበት *የሁለትዮሽ* ግኑኝነት እና በሕብረት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡**

በአምልኮ ወቅት እግዚአብሔር ይናገረናል ደግሞ ይሰማናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል አማካኝነት አምላካችን ይገሥጸናል ያፅናናናል እንደዚሁም ያነቃናል ፡፡ እኛ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ሚዳት እያደመጥን በምስጋናና፤ በንሰሀ፤ በምልጃ፤ በምስክርነት እንዲሁም በማስጠት ምላሽ እንሰጣለን፡፡ እግዚአብሔር በሚያቋርጥ መልኩ ሕዝቡን በመቀስቀስና ከሕዝቡ ጋር ግኑኝነት በማድረግ እንዲሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ጤነኛ ግንኙነት ሲኖረን ሚዛኑን የጠበቀና በአትኩሮት ወደ ማድመጥና እዉነትን ደግሞ ወደ መናገር ልምምድ ወስጥ እንገባለን፡፡ ጤናማ አምልኮም ልክ እንደዚሁ ነው፡፡ ለዚህም ነው በአምልኮ ላይ የቃላችን ትክክለኛነት ግድ የሚለው ቃሎቻችን እግዚአብሔር ጉባኤዎን ለመናገር ይጠቀምባቸዋል በቃላችን ደግሞ ምስጋናችንና ፀሎታችን ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን፡፡

**3. የክርስቲያን አምልኮ *በቃል ኪዳን* ላይ የተመሰረተ ነው፡**

በአምልኮ የእግዚአብሔር መልካምነትና ከእኛ ጋር በክርስቶስ በኩል የገባዉ አዲሱ ቃልኪዳን ታድሷል፣ ታወጆአል ፣ታትሟል፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሊኖረን ወደሚገባ መልካም ሕብረት የጠራን በሚያስገድድ የወል ስምምነት ሳይሆን ራሱን በፍቅር አሳልፎ በሰጠ፣በተስፋ በተመሰረተ ቃል ኪዳናዊ ሕብረት ነው እንጂ፡፡ ይህም እንደ ሕጋዊ የወል ስምምነት ሳይሆን እንደ ጋብቻ ቃል ኪዳን ስምምነት ዓይነት ነው፡ አምልኮ የእግዚአብሔርን ተስፋ የምናስተወልበትና ራሳችንንም ለቃል ኪዳናዊ ግኑኝነታችን አሳልፈን የምንሰጥበት ነው፡፡ በማንኛውም የአምልኮ አገልግሎት ማቃሰብ የሚኖርበት ጉዳይ ቢኖር አምልኮው እንደ ታማኝና ቃል ኪዳኑን እንደጠበቀ ወዳጅ ከእግዚአቤሔር ጋር ለመነጋገር የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለወን ነው፡

**4. የክርስቲያን አምልኮ *የሥላሴን ትምህርት መሠረት ያደረገ ሊሆን* ይገባዋል፡፡**

በአምልኮዋችን ልንደርሰው የሚገባው በአንድነቱና በሦስትነቱ ታወቆ የሚኖረው -እግዚአብሔር አብ፤እግዚአብሔር ወልድ፤እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ነው፡፡ እርሱም በማለኮት አንድ በአካል ሦስት የሆነወን ቅዱስ አምላክ፣ የፍቅር አምላክ፣ ውብ አምላክና ሃይለኛ አምላክ ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱ ነው በፀጋዉ ወደ አምልኮ የሚጋብዘንና ምላሻችንንም የሚያደምጠው፡፡ እግዚአብሔር ራሱ ነው ፍፁማን የሚያደርገን ምስጋናችንና ልመናችንንም የሚሰማልን፡፡ በሰማክ ው ላይ ሚዳት እንዲኖረን የሚያግዘንና ምላሽ ደግሞ እንድንሰጥ የሚያበረታታን እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እንግዲህ በአምልኮ ሕብረት እንድናደርግ የምንጋበዘው ከእግዚአብሔር አብ ጋር በእግዚአብሔር ወልድ በኩልና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡ አምልኮ በእወነት፣እንዲሁም ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች አማካኝነት፤ ለምሳሌ በጥምቀተ ወሃ፣በሕብስትና በወይን ደግሞም በሚዚቃ ቃና፣በሕብረት፣ በሰወነት እንቅስቃሴ፣በፈገግታ እና ሰላሞታ በማለዋወጥ ሳይቀር በአንድነትና በሦስትነት ወደ ሚሟለከው እግዚአብሔር ቀርበን የምንመገብበትና የምንመካርበት ሥሬዓት ነው፡፡ በአምልኮዋችን ትኩረት የምናደርገው ራሱን አሳልፎ በሰጠን በእግዚአብሔር ላይ ነው፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ አምልኮ በአምልኮ እንቅስቃሴዎቻችን ላይ ብቻ በማትኮር እንዳንወሰደ ይጠብቀናል፡፡

**5. የክርስቲያን አምልኮ *ማህበራዊ* ነው፡፡**

የክርስቶስ ወንጌል ከሌሎች ሰዎች ጋር ሕብረት እንዲኖረን አስችሎናል፡፡ አምልኮ የቤተ ክርስቲያንን ዕምነነት በተግባር የሚገለጽበት አንድነታችንን ቅድስናንና የቤተክርስቲያን ምስክርነትን ጎልቶ የሚወጣበትና ጥልቀቱም የሚለካበት ነው፡፡አንፅኦት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ቢኖር በአምልኮ በሚያስደንቅ ሁኔታ የተለያየ ማንነት ያላቸው ሰዎች በአንድነት ያመሰግናሉ ፣በአንድነት ይፀልያሉ፣ በአንድነት

እግዚአብሔርን ይሰማሉ ፣በአንድነት ቃል ኪዳን ደግሞ ይገባሉ፡፡ስለዚህ አምልኮ የሁላችንም አስተዋፅኦ ወጠቷ ነው፡፡

### 6. የክርስቲያን አምልኮ ለሌሎች *የሚራራ የሚጠነቀቅና ሌሎችን የሚጋብዝ* ሊሆን ይገባዋል፡፡

የክርስቲያን አምልኮ በክርስቲያኑ ላይ ብቻ ያተኮረ ሊሆን አይገባም፡በአምልኮዋችን ለዓለሙ ሁሉ መፀለይ እንዲሁም ደግሞ በፍርሃት ያሉትን፣የሚጨቁትና በብቸኝነት ለሚኖሩት ሁሉ እርኅራሔን ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡የሕብረት አምልኮ ሌሎችን እንድናገለገል፣ ምስክር እንድንሆን፣ በአምልኮ ሕይወት እንድንኖርና ወደ ሌሎች ደግሞ እንድንላክ የሚያደርገን ነው፡አምልኮ በወንጌል ተስፋዎች የሚፅናናን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ይህ ዓለም ምን ያህል የተበላሸና በፍርሃት የተሞላ እንደሆነ እንደዚሁም ይህ አለም ደግሞ ምን ያህል አዳኝ እንደሚያስፈልገው እንድንገነዘብ በሚድረግ ሃላፊነት እንዲሰማንም የሚያደረግ ነው፡አምልኮ ይህ የወደቀዉ ዓለም ከጥፋት እንዲድን እንድናገለግል የልባችንን መሻት የበለጠ የሚያቀጣጥል ነው፡፡

### 7. የክርስቲያን አምልኮ “በአለም ውስጥ ነገር ግን *ከአለም ያልሆነ*” ሊሆን ይገባዋል፡፡

የክርስቲያን አምልኮ ሁልጊዜ ባህልን ያንፀባርቃል፡፡ የንግግር ዘይቤን፣አለባበስን፣የሰዓት አጠቃቀምን፣ የሕይወት ልምድንና የሙዚቃ ውህደት እና ስዕላዊ ማለጫዎች ሁሉ እንደ የባህሉ አወድ ይለያያል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ አምልኮ በባህል ተጽዕኖ ወስጥ ሊወድቅ አይገባም፡በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ከባህል በላይ በመሆን የነብይነት ተግባሩን ሊፈፅምና ተገቢ ያልሆኑ ባሕሎችንም ሊኮንን ይገባዋል፡፡

### 8. የክርስቲያን አምልኮ *በለጋሥነት ፍፁም በሆነ ሁኔታ እኛነታችንን በእግዚአብሔር ፊት የምናፈስበት ሊሆን ይገባል፡፡*

አምልኮ አሰልቺና አድካሚ መሆን የለበትም፡ ይልቁንስ ልክ እንደዛ በጌታ ኢየሱስ እግር ላይ እንደፈሰሰው ሽቱ የሚያወድ መአዛ ያለው መሆን አለበት፡፡አምልኮዋችን ለፈጠረንና ላዳነን አምላካችን ከልብ በመነጨ ፍቅርና የምስጋና ዝማሬ ያለመቆጠብ የሚቀርብ ሊሆን ይገባል፡፡ አምልኮ ምርጥ የሆነውን ነገራችንን ለእግዚአብሔር እንድንሰዋ ነው የሚጋብዘን፡፡ መዝሙር ስንለማመድ፣ ቃሉን ለማስበክ ስንዘጋጅ፣ገንዘባችንና ጊዜያችን መስዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ጭምር የሚደረግ ተግባር ነው፡እንዲሁም አምልኮ ለእግዚአብሔር በማየት እኛነታችን አሳልፈን በመስጠት ባረፈና በተዘጋጀ ልብ ሊፈፀም ይገባል፡፡ የግል አትኩሮታችን ሁሉ ስብስብ በሚድረግ አምልኮዋችንን ማቅረብ ይጠበቅብናል፡፡ የምናመልከው ክብር የተገባው ታለቁን አምላካችን ነውና፡፡ ስለዚህ በነቃና በሚስተዋል መንፈስ እንድናመልክ ይጠበቅብናል፡፡

### 9. የክርስቲያን አምልኮ *ገላጭና የሚቀርጽ* ሊሆን ይገባል፡፡

አምልኮ ማህበረሰቡ የተለማመደውንና የሚያወቀው እውነታ በታማኝነት የሚገልጥ ሊሆን ይገባል፡፡በመዝሙር ዳዊት እንደተገለጠው በነቃ መንፈስ በታማኝነት ዝማሬንና እንባን፣ምስጋናንና ንሰሀን በመግለጥ የሚያሳይ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አምልኮ የእኛ የራሳችን ቃል ያልሆነ ለምሳሌ

እንደ “ጌታ ፀሎት” የማሳሰሉትን በማከል ከጌታ ጋር ባለን ግኑኝነት እኛን በመቅረፅ ወደ አዲስ ጠለቅ ወዳለና ከእግዚአብሔር ጋር ሕይወት ወደ ምንካፈልበት ሊያዘልቀን የሚችል ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ስናመልክ የምንሰማው ቃል በመንፈስ የተሞሉ የደቀመዝሙርነት ሕይወት መሣሪያ ይሆናል በተጨማሪም ለጌታ ምስክር እንድንሆንና በባህሪይ የተቀረጽን ታማኝ የጌታ ተከታዮች ያደርገናል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአምልኮ ደንቦች ምሳሌያዊ ናቸው እንጂ ፍፁማን መመሪያዎች አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ ለሁለት ሺህ ዓመታት የዘለቀወን የክርስቲያን አምልኮ ምንነት የሚያስረዱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ መሠረታዊ ደንቦች በጣም አስፈላጊ ከመሆናቸው የተነሳ እንደ መጽሐፍ መግቢያነት ተቆጥረው ሊተወም አይገባም፡፡ይልቁንስ በየሳምንቱ አምልኮ ለመምራት በሚዘጋጁ የአልምኮ መሪዎች ልቦና ሊያቃጭሉ ይገባል እንጂ፡፡በየሳምንቱ ለሚከሄደው አምልኮ ሥርዓት ሃላፊ የሆኑ ሰዎቸ በሙሉ በደስታ ተልዕኮዎቸወን ለማከካት አምልኮ በእወነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣እግዚአብሔርም ሰወም የሚፔገርበት፣ ቃልኪዳናዊ፣ ሥላሴን ያማከለ ለሌሎች የሚራራ፣ ገላጭና የሚቀርፅ ግሩም የሆነ እንዲሆን ሊጥሩ ይገባል፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ደንቦች በአንድነት እንዲገለጡ ልናስብበት የሚገባ ሥፍራ አለ፡፡ የክርስቲያን አምልኮ በአንድ ጊዜ ሥላሴን ያማከለና የሚራራ፣ቃልኪዳናዊና በአለም ወስጥ ሆኖ ነገር ግን ከአለም ያልሆነ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ ምርጫ ሚድረግ ይጠበቅብናል አልያም የስነመለኮት እይታችን ርህራሄ የሚጠይቀወን ዋጋ በመክፈል ማስፋት ወይም የስነመለኮት እይታችንን በርሕራሄ ስም ማደከም ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ ጹሁፍ የተገለጹት ጠቃሚ ሀሳቦች ለማህበረ ምዕመናን ምሳሌ እንዲሆኑ ታቅዶ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ደንቦች የሚሰሩ መመሪያዎች አድረገን ስንወስዳቸው የትኛው ልምምድ በአወዳችን መሰረት አምልኮዋችንን ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል ሚዳት እንዲኖረን ያግዛል ልንጠይቅዉ የሚገባን ነገር ቢኖር በዚህ ጹሁፍ የተገለፀት ሀሣቦች በአጠቃላይ ከደንቦቹ የፈለቁና የማህበረ ምዕመናናችን አምልኮ መጽሐፍ ቅዱሰአዊ ሚዘን እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸወን? በግኑኝነት ላይ የተመሰረተ ነዉ ወይ? እግዚአብሔርን የሚያከብር ነው ወይ? የሚያንፅ ነው ወይ? የሚሉት ይሆናል፡፡

## ለሚያመለክና አምልኮን ለመምራት መዘጋጀት

ምናልባት እርሶ የአምልኮ ኮሚቴ ወይም የአምልኮ ዕቅድ አወጪቡድን ይሆኑ ይሆናል፡፡ወይም ቤተክርስቲያናችሁ መጋቢ የላትም ይሆናል፡፡ ስለዚህ እርስዎ የእሁድ አምልኮ በሚመለከት ጉዳዮች እንዲያዘጋጁ ተመርጠዉ ሊሆን ይችላል፡፡ምናልባትም ደግሞ እርስዎ መጋቢ ወይም የስነመለኮት ትምህርት ቤት ተማሪ ይሆኑ ይሆናል፡፡ወይም አምልኮን በተመለከተ ያሉትን ግንዛቤ ለማሻሻል የሚጥሩ ሰዉ ይሆኑ ይሆናሉ፡፡ምናልባትም እርስዎ የኮሌጅ ተማሪ ሆነዉ የኮሌጅ የተማሪዎች ሕብረት አምልኮ ለመምራት ያቅዱ ይሆናል፡፡ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ አምለኮ ለመምራት የሚዘጋጅ ሰዉ ይሆኑ ይሆናል፡፡ወይም ደግሞ አምልኮን በሚመለከት የብዙ ዘመን ልምድ ያካበተ ሰዉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ነገር ግን ምንም ዓይነት ሰዉ ይሁኑ ይህ መጽሐፍ አምልኮን ለመምራት በሚያደርጉት ዝግጅት እገዛ እንዲያደርግ ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡

እርገጥ ነዉ ይህ መጽሐፍ የሚይዳስሳቸዉ ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ነገር ብቻ ብናነሳ፤ የአምለኮ መሪ የሆነ ሰዉ ሊያሟላቸዉ የሚገባ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ አያካትትም፡፡የእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላ መሆን፣በመንፈስ በመነዳት ስለሚያመልክ ሕይወት፣የመጽሐፍ ቅዱስ ዕወቀት ያለዉ መሆንና ሥነመለኮት ሚዳት ያለው፣ለማሕበረ ምዕመኑ ወይም ለማህበረሰቡ ፍቅር ያለው፡፡እነዚህን ሁሉ አይተነትንም፡፡ ሌላ ምሳሌ ደግሞ ብንጨምር፤ ይህ መጽሐፍ የእያንዳነዱ ማሕበረ

ምዕመን የአምልኮ ዕቅድ ስለማውጣት ሂደትም አይዳስስም ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ የተለያየ አመለካከት ያላቸዉ ብዙ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት አሉና፡፡ሆኖም ይህ መጽሐፍ ልንጠቀምበትና ደግሞም የራሳችን ልናደርገዉ የምንችለዉ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች ይሰጠናል፤እንደዚሁም ቁልፍ የሆኑ መሠረታዊ የአምልኮ ዋና ሐሳቦች ያነሳልናል፡፡በተጨማሪም አምላኮን በተመለከተ አዳዲስ አቀራረቦችን በመዳሰስ ያስተዋውቀናል፡፡ሆኖም የዚህ መጽሐፍ ጠቃሚነት ለማሙላት የአምላኮ መሪና የአምልኮ ዕቅድ አወጪዎች ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

*የአምልኮ ዕቅድ አዉጪ እንደ ካህንና ነቢይ*

እንደ አምልኮ ዕቅድ አወጪነታችን በጣም አስፈላጊ ደግሞም አስፈሪ ተግባር እንፈጽማለን፤ይህም በሕዝቡ አንደበት ላይ በፀሎት የሚገለጡ በሌላም ሚልኩ የሚገለጡ ቃሎችን እናኖራለንና፡፡ይህም መዝሙር ስንመርጥ ወይም በጽሁፍ የሚነበብ ፀሎት ስንጽፍ ሁልጊዜ የሚሆን ጉዳይ ነዉ፡፡እንደ አምልኮ ዕቅድ አወጪነታችን፣ደግሞም ካህናት ነንና የእገዚአብሔርን ሕዝብ ፀሎት እንቀርጻለን፡፡ልክ የብሉይ ኪዳን ካህናት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክሉ እንደነበረ እንደዚሁም በዚህ ዘመንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ፀሎት ቅርጽ እናሲዛለን፡፡

እኛ ቅዱስ የሆነዉን የእግዚአብሔርን ቃል የማገልገል ሃላፊነት ተቀብለናል፡፡የዕለቱ የእግዚአብሔር ቃል ስንመርጥና የምንመርጠዉም ዋና ሀሳብ በእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊ አመጋገብ ላይ፤ደግሞም የሕይወት እንጀራን እንዴት እንደ ሚመገቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ባለን ሚዳት ላይ ማጠነኛ ተፅእኖ ለማሳደር ነዉ፡፡እንደ አምልኮ ዕቅድ አወጪነታችን የትኛዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልና ዋና ሐሳብ ለዕለቱ አምልኮ ማዕከል እንዲሆን ስንወስን ሁሉ የነቢይነት ሚና እንጫወታለን ማለት ነዉ፡፡የብሉይ ኪዳን ነብያት የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ያደርሱ እንደነበር በዚህ ዘመንም በጹሁፍ የተገለጠዉን የእግዚአብሔርን ቃል ማሕበረምዕመኑ የሚሰማበት መንገድ እንቀርጻለን፡፡

ስለዚህ የአምልኮ ዕቅድ አወጪዎች የክሕነትና የነቢይነት ሚና ይጫወታሉ ማለት ነዉ፡፡በክርስቲያን ማህበርምዕመናን እነዚህ ሚናዎች ዋና ጉዳይ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እ አምልኮዋችንና እኛ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ምላሽ አግባብነት ያለው እንዲሆን የሚቀርጹ ናቸዉና፡፡የስነ መለኮት ምሁራን የተሜሩ ክርስቲያኖችን ስነመለኮታዊ ግንዛቤ የሚቀርጹ መጽሓፍትን እንደሚጽፉ ሁሉ የአምልኮ ዕቅድ አወጪዎችም ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የአምልኮ አገልግሎት ስነመለኮት የሚቀርጽ ሥራ ይሰራሉ፡፡

በዚህ ምክንያት የአምልኮ ዕቅድ አወጪነት የኛን አተኩሮት የሚስብ፣ጥረት የሚጠይቅና የሚሞርክ ሃላፊነት ነዉ፡፡ይሁን እንጂ አንዳንድ የአምላኮ ዕቅድ አወጪዎች የአምልኮ ዕቅድ አወጪነት የአጭር ጊዜ የስልክ ንግግር አድርገዉ በመቁጠር ትልቅ ስህትት ይፈጽማሉ፡፡ ምናልባት አንዳንዴ በአጭር ጊዜ ዝግጅት እንደየ አዉዱ ጥሩ ዕቅድ ሊሆን ይችል ይሆናል፡፡ይሁን እንጂ እንደዚህ ዓይነት ዕቅድ ለትክክለኛ አምልኮ ፍትሐዊነቱ አጠራጣሪ ነዉ፡፡ማጠየቅ ያለበት "እንዴት በፍጥነት እንዳቀድነዉ ሳይሆን" ነገር ግን መሆን ያለበት "እንዴት ነው ይህ አገልግሎት በታማኝነትና በልዩ ሁኔታ የዕለቱ ቃል ሕይወት የሚሰጠው?" የሚለው ሊሆን ይገባል፡፡ሊታሰብበት የሚገባው እንዴት ነው ይህ አገልግሎት በታማኝነትና ትርጉም በሚሰጥ ሚልኩ የዕለቱ የአምልኮ ታዳሚዎች በሙሉ ወደ አምልኮ ሊጋብዝ የሚቻለው? "እንደ ካህንና ነብይ እንዴት አድርገን ነው በታማኝነትና በልዩ ሁኔታ የአምልኮ ማህበረሰባችን የምናገለግለው?"

*የአምልኮ ዕቅድ አወጪነት መልካም ባሕሪያት*

የተዋጣለት የአምልኮ ዕቅድ አዉጪ የሚያደርገን ምንድር ነው? በዚህ አገልግሎት ውጤታማ የካህንነትና የነቢይነት ሚና እንዲኖረን ምን ያስፈልገናል? ሥራውን ለሚጸም ፈቃደኝነት ያስፈልገን ይሆን? ትልቅ መጽሐፍት ቤት ያስፈልግ ይሆን? ጥሩ አቀናባሪ መሆን ያስፈልግ ይሆን? እነዚህ መሣሪያዎች የሚያስፈልጉ ቢሆንም ቅሉ፤ ለክህነትና ለነቢይነት አገልገሎት ሚና በጥልቀት የሚጠቅሙ አይመስለኝም፡፡

እስኪ የሚከተሉትን መልካም ባሕሪዎች ደግሞ እንመልከት፡-

- ከአምልኮው ማህበረምዕመኑ የሚፈልገውንና የሚያስፈልገውን ርሕራሄ አገልግሎት ሚድረስ የሚችል፡፡
- ማን ነው አምልኮን ለመምራት ፀጋ ያለውና በምን መልኩ ነው የሚመራው የሚለውን የማየት ብቃት ያለው፡፡
- ከአምላኮ ዕቅድ አዉጪ ቡድን ጋርና ከአምላኮ አመራር ሰጪ አካል ጋር በመተባበር የመሥራት ችሎታ ያለው፡፡
- ማህበረምዕመኑ ለመስማት የሚችለውን ቃል ለማቅረብ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ያለውና የአምልኮ ማህበረሰቡን በሚገባ የሚረዳና የመጋቢነት አገልግሎት ማስጠት የሚችል፡፡
- በአምላኮ ሂደት በሕዝቡ ወስጥ ሊፈጠር የሚችለዉን ስነመለኮታዊና ስነልቦናዊ ግጭቶች ሚረዳት የሚችል ጥበብ ያለው፡፡
- ቃሉን ለማቅረብ፣ መዝሙሮችን ለማዘጋጀት፣ ተዘጋጅቶ ፀሎትን የመጸለይ እንደዚሁም ማሕበረምዕመኑ በሃይልና ትርጉም ባለው መልኩ ሊያሳትፍ የሚች ልዩ ፀጋ ያለው፡፡
- ከልክ ያለፈ ፈጠራን ወይም እንዳው የወረደ አቀራረብ ይዞ እንዳይቀርብ በነገር ሁሉ ራሱን የሚገዛ፡፡ ምክንያቱም የአምልኮ ዕቅድ መንደፍ ማለት የስነጥበብ ወይም የስነግጥም ዘዴ ማጠቀም ማለት አይደለም፡፡እኛ የምናቅደው ለአምልኮ የሚሰበሰብን መህበረሰብ የሚደርስ መንፈሳዊ ተግባር ነው፡፡ ከልክ ያለፈ ስነጥበብ ስንጠቀም ማህበረሰቡ ተቋቁሞ ላይዘልቅ ይችላል፤ምክንያቱም የትኛዉንም ማህበረምዕመን ፈጠራ በሆነ ቅንብር መጸለይና ከልቡ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እጅግ ያዳገተዋልና፡፡በሌላ መልኩ ደግሞ በጣም የወረደ የአምልኮ አቀራረብ ጉባኤዉን ያዳክመውና ምላሽ የሚይሰጥ ጉባኤ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአምልኮ ዕቅድ አዉጪ ባሕሪያት ላይ ትኩረት አድርገዉ የሚያቅዱት ናቸዉ አምልኮን ትልቅና ትርጉም የሚሰጥ የሚያደርጉት፡፡ ምናልባትም እነዚህ ዝርዝሮች ያልተሟሉ ሊመስለን ይችል ይሆናል፡፡ማስታወስ ያለብን ግን ማኛችንም ብንሆን በተፈጥሮ ሁሉንም መልካም ባሕሪያት የሌለን መሆኑን ነዉ፡እንደዚሁም ደግሞ ማንም ሰዉ ሁልጊዜ በእነዚህ ባሕሪያት መኖር አይችልም፡ ሆኖም የአዲስ ኪዳን መልካም ዜና እንደ ሚያበስረን እነዚህ መልካም ባሕሪያት ለማለበስ መጣር ብቻ ሳይሆን አማኙን ማሕበረሰብ ለማነጽ የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታ መሆናቸውንም ማወቅ ጭምር ነው፡፡እንደ አምልኮ ዕቅድ አዉጪነታችን መጀመሪያ ልናደርገው የሚገባ ነገር ቢኖር በፀሎት እነዚህ ስጦታዎች በሕይዎታችን እንዲገለጡ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው፡፡የትኛዉንም የጎደለ መልካም አሰራር ቢኖር ወደ ማህበረምዕመኑ በመመልከት ያንን ፀጋ ያለዉን ሰዉ በሚፈለግ ፀጋው እንዲያካፍል መጋበዝ ነው፡፡

የአምልኮ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ አምልኮን መምራትና በኋላም መገምገም ብዙዎችን በጥልቀት የሚያሳትፍ ነው፡፡ አምልኮን ለማቀድ የምንጠቀምባቸዉ መጻሐፍት፣ የመዝሙር ደብተሮችና ሌሎች ምንጮች ጥቅማቸዉ አነስተኛ ቢመስልም ነገር ግን በጣም አስፈላጊ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡በእዉነተኛ የክህነት አገልግሎት የሚገለጥ ፀሎት ከእወነተኛ የፀሎት ሕይወት የሚገኝ ነው፡ ሆኖም አንዳዴ ደግሞ ይህም ቢሆን የአምልኮ

ጉባኤያችንን በጣሣ ወደ ፀሎት ወስጥ እንዲገባ ላይረዳን ይችል ይሆናል፡፡ስለዚህ ከሌሎች ደግሞ በተለይም ከመጽሐፍ ቅዱስ፣በሌላ ቦታና ጊዜ ከተደረጉ የአምልኮ ጉባኤዎች የምንቀስመው መልካም ነገር ይኖራል፡፡

ለዚህም ነው በተለያየ ቦታ የተዘመሩ መዝሙራት፣የመዝሙር መጽሐፍትንና ስብስብ የፀሎት መጽሐፍቶች ማጠቀም የሚያስፍልገን፡፡ ስለዚህ እያንዳነዱ ማህበረምዕመን የሚጠቀምበት መዝሙሮችና የመዝሙር መጽሐፍት ማዘጋጀት ቢችል መልካም ነዉ፡አንዳንደም ለማጠቀም የምናዘጋጃቸው መዝሙሮች ከደራሲው ደምፀ ቀላጼ ወይም የሚዚቃ አጠቃቀማቸን ሊለይ ይችል ይሆናል፡፡

ለዚህም ነዉ መጽሐፉ ሲዘጋጅ በትክክለኛ ቅላፄው ማዘጋጀት የሚስፈልገን፡፡ እነዚህ የሚዘጋጁ መጽሐፍት በተለያየ ጊዜና ቦታ የተከናወኑ የአምልኮ ጥበብ ያሰተምሩናል፡፡እያንዳንዳችን በግል ከምናደርው አምልኮ ይልቅ ሰፋ ባለ ዕይታ አምልኮአችንና ምስጋናችንን እንድንሰዋ ያግዙናል፡፡ዝሜሬወም በሚዚቃ ታጅቦ ሲቀርብ የዝሜሬው ቃል ልክ የራሳችን እንደሆነ አድርገን እንዘምረዋለን፤እንደዚሁም ደግሞ በጉባኤያችን ካለ አንድ አስፈላጊ ጉዳይ ጋር እንዲዛመድ በቋንቋችን ትርጉም እንሰጠዋለን፡፡የራሳችንም ደምፀ ቅላጼ በማጠቀም የምንዘምረዉ ቃል ዋጋ ያለዉ እንዲሆን እናደርጋለን፡፡

ለአምልኮ ዕቅድ አወጪ የሚያስፈልጉን መልካም ባሕሪያት ባይሆኑም እንኳ በዚህ መጽሐፍ ወስጥ የተጠቀሱት ግብዓቶች የአምልኮ ዕቅድ አወጪዎችና መሪዎች የክህነትና የነቢይነት አገልግሎታቸወን በታማኝነት እንዲወጡ ይረዳሉ የሚል ዕምነት አለን፡፡

በአንዳንድ ባሕሎች የአምልኮ መሪዎች በጋለ ስሜት እንዲመሩ ይበረታታሉ፤በሌላ ባህል ደግሞ ለስሜት ምንም ቦታ የሚይሰጥበት ሁኔታ ያጋጥሚል፡፡በአንዳንድ ባህል ደግሞ የአምልኮ መሪዎች በጽሁፍ የተዘጋጀ ፀሎት እንዲፀልዩ ይገደዳሉ በሌላው ደግሞ የአምልኮ መሪዎች ያለዝግጅት እንዳመጣላቸው እንዲፀልዩ ይፈቀድላቸዋል፡፡ይህ መጽሐፍ ደግሞ እነዚህን ሁሉ ባካተተ መልኩ እንዲያገለግል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡ ከአምልኮ መሪዎች የሚጠበቀው ዋና ነገር የትኛው ለየትኛው ዓይነት ክርስቲያን ማህበረሰብ ወጤታማ በሆነ መልኩ ሊጠቅም እንደሚችል ለይቶ ሥራ ላይ ማዋል መቻል ነው፡፡

**የአምልኮ ጊዜ ቃሎቻችን**

በእርግጥ አምልኮ ከቃል በብዙ ያለፈ ነው፡፡ይሁን እንጂ በአምላኮ ጊዜ በአብዛኛው ብዙ ቃላቶች ጥቅም ላይ ይወላሉ፡፡በርግጥ አንዳንድ ጊዜ በፀጥታ ሆነን በማሰላሰል ወይም በሚዚቃ ቅንብር ብቻ ከቃሎች ወደ ሚበልጥ ተማስጦ ልንገባ እንችላለን፡፡ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን አምልኮ አብዛኛው በቃሎች ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

ስለድነት ጉዳይ ቢሆን፣ስለራሳችንና ስለእዚአብሔር ልናወቀውና ልንናገረው የሚገባን ግንዛቤ ሁሉ እንኳ ቢሆን በፍጥረታት ብቻ አልተገለጠም ነገር ግን በእግዚአብሔርም ቃል ጭምር ነው እንጂ፡፡የሕብረት አምልኮዋችን እንኳ በራሱ ወጤታማ የሚሆነው እርስ በርሳችን መነጋገር ስንችል፣እንድናመልክ ስንሰበሰብ፣ለእርስ በርሳችን የጋራ ፀሎቶች ተከፋፍለን ስንፀልይና አንዳችን ለአንዳችን በእምነታችን እንድናድግ ስንበረታታ ነው፡፡ይሁን እንጂ አብዛኛወን ጊዜ በሚዚቃ የምንሳበወን ያህል እንኳ ለእርስበርሳችን በቃል መነጋገር ብዙም ትኩረት አንሰጠውም፡፡ ልብ ብንል በየዓመቱ እርስበርስ ለመነጋገር የምንሰጠው ጊዜ ለመዝሙር ከምንሰጠው ጊዜ በአብዛኛው ያነሰ ነው፡፡በእርስበርሳችን መካከል የሚደረግ መነጋገር እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ቆጥረን ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ የአምላኮ ሥርዓት በራሱ መልካም ባሕሪ አይደለም፡፡ ነግር ግን የበለጠ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ቢኖር በእርስ በርሳችን መካከል

ለማብረታታት ሌላወን ደግሞ ለሚድመጥና በእርሱ ጉዳይ ተካፋይ በማሆን ወቅታዊ ፀሎት መፀለይን በመካከላችን እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ ይገባል፡፡

አብዛኛወን ጊዜ ተግዳሮት የሚሆንብን ጉዳይ ቢኖር የአምልኮ ጊዜ የሚዋጠው የሁሉንም ሰዎች አምልኮትና ፀሎት በሚገልጠው በጥቂት ሰዎች ቃሎች መሆኑን ነው፡፡ በሚያመልኩ ሰዎች ዕይታ ሁልጊዜ የአምልኮ ቃሎች ከጥቂት ሰዎች በኩል የሚቀርብ ነው፡፡ አምልኮት አቅራቢዎች ሁልጊዜ አንዱ ሰው በሚያቀርበው ቃል እናመልካለን፡፡ ይህንንም ቃል ደግሞ የመሚር ፈጣን ግንዛቤ ደግሞ አለን፡፡ይህን ግንዛቤ ደግሞ ለየት ያለ የሰው ልጅ የግንዛቤ ችሎታ ያዘለ ነው (ማህበረሰቡ የሰጠንን ቃል ተቀብልን በእምነት እንሄዳለን፤ቃሉ እንኳ በትክክል ባይቀርብ ጥርጣሬን ታግሰን በፀጋ እንወጣለን፤የሰማነወን ቃል ከራሳችን ጋር የማዋሃዱ መሻት ደግሞ አለን)፡፡

በእርግጥ የአምልኮ አገልግሎት ዕውነታ እያንዳንዱ የማህበሩ አምልኮት አቅራቢ በንቃ ማንፈስ ከልብ በአዕምሮ በነፍስ፣በፈቃድና በዕውነትም ለተነገሩት ሚልካም ቃሎች ሁሉ በማስጠት የተሳፍ እንደሆነ ነው፡፡ሆኖም መዝሙሮ የዘሚረ ሁሉ ከልብ በአዕምሮና በፈቃድ በሁሉ ተሳተፎአል ላያስብል ይችላል፡፡ የመማስጥ ማጠን ምናልባትም አንዳንዴ በሰውነት እንቅስቃሴ ሊገለጥ ይችላል፡፡ ይህም ቢሆን በቂ ላይሆን ይችላል፡፡ ምንም እቅስቃሴ ያላሳየሰው ደግሞ ምናልባት በወስጡ በጣም ተነክቶ ሊሆን ይችላል፡፡ምናልባት አንዳነዶች በጣም የሚንቀሳቀሱት የሚዚቃ ወበት ስቦዋቸው የቃሉ አገላለጽ አደናቂ ሆነው እንጂ በአምልኮ ተነክተው ላይሆን ይችላል፡፡ሆኖም ልክ እንደ ሚዚቃ ወበትም የአምልኮ ቋንቋ ግብም ማህበሩ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ የሚስብ የሚያነሳሳ ሊሆን ይገባል፡፡ በአርግጥ ይህ ግብ አብዛኛወን ጊዜ አይጨበጥም፡፡ ይሁን እንጂ ምሳሌ የሚሆኑንም በመሜልከት በጊዜ ሂደትም ቢሆን አምልኮዋችን በሚገባ ቃል መቅረጽ የተገባ ነው፡፡ በአምልኮ ወቅት ስለምንጠቀምባቸው ቃላት በተመለከተ የሚከተሉት ሦስት ግቦችና ማስፈርቶች መሜልከት ይጠቅሚል፡-

**1. ቃላችን ለክርስቶስ ወንጌልና ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝ የሆነ መሆን አለበት**

የዚህ ክፍል ከፊል ግብ የተመጣጠነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዋና ዋና ሀሳቦች በመዳሰስ መናገር ይሆናል፡፡ ስለእግዚአብሔር ስንናገር አምላካችን ታላቅ ንጉሥ፣ ሩህሩህ ደግሞም አጽናኝ መሆኑን ማንዘብ ያስፈልጋል፡፡ደግሞም ስለጌታ ኢየሱስ ስንናገር አዳኝና ጌታ መሆኑ መግለጽ ይገባናል፡፡ይህ ብቻ አይደለም በክርስቶስ ድነት በፍጹም የግል ቢሆንም ነገር ግን ይህ የማዳን ሥራ ወደ ፍጥረት ሁሉ የዘለቀና ባህልን ሁሉ ተሻጋሪ መሆኑን ማንዘብ ያሻል፡፡ስለቤተክርስቲያን ደግሞ ስንናገር ልገልጸው የሚገባ ነገር ቢኖር የአማኞች ማህበር መሆንዋን፣ደግሞም ቸርነት አድራጊና ዕውነትን የምትገልጥ፣የክርስቶስን ወንጌል የምታብሥርና በምድር ላይ ሰላምና ፍትህ እንዲሰፍን የምትሠራ መሆንዋን ሊሆን ይገባል፡፡

በተለይም በኛ ዘመን ስለእግዚአብሔር የምንናገርበት ቋንቋ ቀጣይነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡በተለይም የእግዚአብሔርን ስሞች፣ስዕላዊ አገላለጦችና በመጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ የተገለጠትን የእግዚአብሔርን ማንነቶች የሚገልጹ ሀሳቦችን በማጠቀም ልንገልጠው ይገባል፡፡ምናልባትም ይህ አባባል ሁሉንም ላያረካ ይችል ይሆናል፤ሆኖም ግን የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በቤተክርስቲያን ወስጥ የሚሱ ወዝግቦችን ሚርገብ ይቻላል፡፡

**2. ማህበረምዕመኑ ሊረዳወና ሊገነዘበው በሚችለው ቃላት ማጠቀም ያስፍልጋል፡፡**

በአምልኮ ወቅት የሚገለጡ ቃላቶች የከበሩና ሕዝቡ በቀላሉ ሊያገኘው የሚችል፤ደግሞም ሊረዳው የሚችለው እንደዚሁም በሕሊናው ተቀርፆ የሚቀር ቢሆን እጅግ ይመረጣል፡፡ በአምልኮ የምንናገረው ቃል

ሁሉንም የማህበረ ምዕመኑ አካል የሆነ ማለትም ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣አዲስ ክርስቲኖች፣ረጅም ዘመን የቆዩ አማኞችን ሁሉ የሚያካትት ሊሆን ያስፈልጋል፡፡

አንዳንድ አብያተክርስቲያናት በእርግጥም ማህበረ ምዕመኑ በአምልኮ እንደሚገባ እንዲሳተፍ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንደዚሁም አምልኮት አቅራቢዎች በሕብረት ፀሎት እንዲሳተፉ ማነሳሳት የቤተክርስቲያን ሥራ ነው፡፡ በእርግጥ ማህበሩ በጥልቀት እንዲካፈል ለማድረግ ጊዜ ይወስዳል፤ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ጉባኤ በንስሀ ፀሎት ጊዜ ማንበርከክን ይመርጣል፣በዝማሬ ወቅት ደግሞ እጅን በማንሳት ማመስገን ይወድ ይሆናል፤ ሌላው ጉባኤ ደግሞ የዕለቱ ቃል ከተነበበ በኋላ አንባቢው “ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው” ሲል ጉባኤው ደግሞ “እግዚአብሔር ይመስገን” በማለት በአንድነት የመመለስ ልማድ አለው ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ በሁሉም ጉባኤ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲለመድ ማድርግ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፡፡ነገር ግን ከብዙ ጥረት በኋላ ሊሳካና ሊጠበቅ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡

## 3. የሚያስፈልገን ሁለቱንም ማለትም ልምድ እንዳለን የሚያሳይና ወደ ጠለቀ ልምምድ የሚከተን የቃላት አጠቃቀምን ነው፡፡

በግልና በማህበር የሚገለጥ ጤነኛ የሆነ የፀሎት ሕይወት በሁለት ዓይነት ፀሎቶች ዙሪያ ያጠነጥናል፡- በመጀመሪያ አንዳንድ ፀላዮች ወስን ናቸው፤በዝግጅት ላይ ያለተመሠረተ፣የግል እና ቅፅበታዊ ፀሎት ነው የሚፀልዩት፡፡ እንደዚህ ዓይነት ፀሎት የሚፀልዩ ሰዎች መነሻቸው ልምምዳቸው ነው፡፡ ለምሳሌ “ ጌታ እግዚአብሔር በዚህ በሚያታምንና ፍርሃት ባለበት ጊዜ ማህበረምዕመናችንን እርዳ…” ሁለተኛ አንዳንድ ፀላዮች የማህበር ፀሎት ላይ ያተኩራሉ ወይም “ የተሰጠ” እንዲያውም በጉባኤው ላይ “ ጮኽ የሚነጥር” ፀሎት ይፀልያሉ፡፡ እስቲ የጌታን ፀሎት ስለሚፀልዩ ልጆች ለአንድ አፍታ ያስቡ፤ምናልባትም ቃሉ ምን እንደሆነ ሳይገባቸው ፀሎቱን መፀለይ ይጀምሩታል በጊዜ ሂደት ግን ትርጉሙ ይረዱታል በዚህም ሁኔታ ያድጋሉ በሕይወታቸውም ዘመን ሁሉ በማሳጠት መፀለይን ይማራሉ፡፡ እስቲ ለአንድ አፍታ ደግሞ አንድ ወንጌላዊ አዲስ ሰው መፀለይ እንዲችል “ይህንን ፀሎት ከእኔ ጋር ፀልይ” ብሎ ሲያለማምድ ያስቡ፤ ወይም ደግሞ ከመዝሙረ ዳዊት መፀለይን ያስቡ፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች የፀሎት ሕይወታችን በራሳችን ሀሳብ፣ልምምድና ስሜት ላይ ብቻ ባለመወሰኑ የታደልን ነን፡፡ ይልቁን ከራሳችን ወደ ሚበልጥ ወደ ትልቅ ነገር የሚጎብዘን ነው፡፡

በአምልኮ ጊዜ ስለሚገለጠውና በዚህ መጽሐፍ ደግሞ ስለተጻፋው ቃል የሚጨነቁ ማስሰቢያ ማለት የምፍልገው ነገር ቢኖር፤በሚዚቃ እንደሚገለጠው ያህል የመጽሓፍ ቃል ያን ያህል ጠቃሚ ላይሆን ይችላል፡፡ ወጠቃሚነቱ ግን ቃሉ ወደ ሕይወት በሚያመጣው ሰው ንግግር ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ አንድ ዓይነት ፀሎት ከተዘጋጀ መጽሓፍ ወይም ከመጠጥፍ ተመረከዞ ማንበብ ሕይወት የሚይሰጥ ወይም ሙት የሆነ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ቃሉ እንዴት ተደርጎ ትቅም ላይ ከማዋሉ ላይ ነው፡፡

በተለይም ይህ ጉዳይ እውነት የሚሆነው ለልጆች ትክክለኛ ቃል ለማቅረብ በምናሳየው ጥረት ነው፡፡ ልጆች ለአምልኮ የሚያበረታቱ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ልጆችን በሙሉ ሃይላቸው በአምልኮ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህም በመልካም ሥራቸው ሊበረታቱ ይገባል፡፡እንግዲህ ይህ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የአምልኮዋችን ቋንቋ ልጆችንም ያካተተና ሊደረስበት የሚችል ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ለልጆች የሚነገር ቃል ዝቅ ያለ ወይም በጣም የተለየ ይሁን ማለታችን አይደለም፡፡ ቃሉ ትክክል ከሆነ በድምፅ ቅላጼያችን እንኳ ለእነርሱ ትርጉም እንዲሰጥ ማድረግ እንችላለንና አብዛኛውን ጊዜ መሪዎች ለልጆች ሲናገሩ የልጅ ንግግር ሳይሆን ልክ አስተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ እንደሚነገሩዋቸው ሊሆን ይገባል፡፡ ልጆች የሕጻን ንግግር ሳይሆን የሚፈልጉት ልጆችን የሚያምጥን ንግግር ነው፡፡ ለልጆች በጣም

ሳይቃለል መናገር ተገቢ ነው፡፡ለዚህም ነው በዚህ መጽሐፍ ወስጥ “ ልጆችን የሚመጥን” ጽሁፍ የተካተተው፡፡ ቃሉ በራሱ በቂ አይደለም ነገር ግን በአክብሮት ለልጆች እንደሚሆን የሚናገረው ሰው ያስፈልጋልና፡፡

**የአምልኮ ሥነ ሥርዓት፡- ከክርስቲያንአዊ ልምምድ ጥበብን መማር**

በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ይህ ነው የሚባል አንድ ወጥ የሆነ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ተጽፎ አናገኝም፡፡ የሆነ ዓይነት የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ያዳበርን እንኳ ብንኖር ፍፁም ትክክል ነው፣መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፣ታማኝና ሕይወት ያለው ነው ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡

የአምልኮ ሥነ ሥርዓትን አስመልክቶ ሊጤን የሚገባው ነገር ቢኖር ወጤታማ የምንለው የአምልኮ ሥርዓት በጥንቃቄ የተዘጋጀና በታማኝነት ደግሞ “ ከላይ በተገለፀው ” መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ከሆነ ነው፡፡ ወጥ በሆነ ሁኔታ የተለመደ የአምልኮ ሥርዓት የተመጣጠነ መንፈሳዊ ምግብ ለማህበሩ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ወጥ የሆነ የአምልኮ ሥርዓት አንዳንድ የሚታቁና በፈጠራ የተካኑ የአምልኮ መሪዎችን የራሳቸውን አጀንዳ ብቻ እንዳያስተናግዱ ያግዳቸዋል፡፡ ከፊት ያለውን እየጠቆመ አምልኮን የሚያስኬድ ሥነ ሥርዓት ማህበረ ምዕመኑ ልቡ ተነስቶ እንዲጠበበቅ ከሚደረጉም በላይ አንዳንዶችና ልጆችንም ጭምር ሁልጊዜ የጉባኤያችን አዘወታሪዎች እንዲሆኑ ያነሳሳቸዋል፡፡

በጣም አስፈላጊ ነገር ቢኖር በትክክል የተቀረፀ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት የአምላኮውን ዋና ዓላማ በሥራ ላይ እንደሚውል ያስረግጣል፡፡በሌላ አባባል በፅኑ ታስቦ የተዘጋጀ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት አምልኮ አምልኮነቱን የጠበቀ እንዲሆን ያግዛል፡፡እንደዚሁም ደግሞ የአምልኮ ሥርዓት አምልኮን የመምራት ማሳሞገሻ ጊዜ ከሚደረግ፣እንደ መዝናኛ ከመቁጠርና የአንዳንዶች ችሎታ ማሳያ ጊዜ ከመሆን ይከላከላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንዶች ዘንድ የአምልኮ ሥርዓት የማያፈናፍን፣ጉባኤን የሚያስርና የፈጠራ ችሎታን የሚቀንስ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ እስቲ የጃዝ ሙዚቃን ልብ በሉ፡፡ ጃዝ ያለምንም ዝግጅት ከወስጥ የሆነ የሙዚቃ እንቅስቃሴን ያፈልቃል፡፡ይሁን እንጂ ጃዝ ተጫዋቹ በሚያቋርጥና ቀጥሎ ያለውን በሚጠቁም መልኩ የተደጋገመ የቅኝት አወቃቀር ላይ አትኩሮ በመጫወቱ ነው፡፡ያለ ቅኝት አወቃቀር ሙዚቃው ቀወስ ፈጣሪ ነው የሚሆነው፡፡ስለዚህ ትረጉም የሚሰጥ ሙዚቃ እንዲሆን ከተፈለገ በሥርዓቱ ተጠንቶ በተዋቀረ ዘዴ መጫወት ያስፈልጋል፡፡

እንደዚሁም ደግሞ ልብ ብለን ከሆነ የአምልኮ ሥርዓቱ በጽሁፍ ይገለጥ ወይም አይገለጽ እያንዳንዱ ማህበረ ምዕመን ቀጥሎ የሚሆነውን በሚጠቁም ዓይነት ሥርዓት የተዋቀረ ነው፡፡ አንዳንድ ማህበረ ምዕመናን በጽሁፍ የተዘጋጀ የአምልኮ ሥርዓትንና ወጥ የሆነ የአምልኮ ልምምድን ይቃወማሉ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት ቀጥሎ የሚሆነውን የሚጠቁም ጠቋሚ ነገር ነው፡፡ የአምልኮ ሥርዓቱ ታትሞ ባይወጣም እንኳ ጥሩ የአምልኮ ዕቅድ አወጭዎችና የአምልኮ መሪዎች የማህበረ ምዕመናቸውን የአምልኮ ሥርዓት በሚረዳት አምልኮውን ወጤታማ እንዲሆን ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ በሁለቱም ማለትም በአምልኮ ሥርዓት አወቃቀርና በአምልኮ ዓይነት ግራመጋባት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በሌጎስ ናይጄሪያ እና በካንሳስ ከፊል ገጠራማ ከፊል ከተማ በሆነ አካባቢ በሚደረግ የአመልኮ ዓይነት በአመራር ልዩነትና በሙዚቃው ባህል ሊለያይ ይችላል ነገር ግን ከስነመለኮት አስተምህሮ አንጻር ደግሞ ስንመለከት አንድ ዓይነት አወቃቀር ሊኖራቸው ይችላል፡፡

እነዚህን ሁሉ ሀሳቦች ያነሳነው በጥንቃቄ የሚዘጋጅ የአምልኮ ሥርዓት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ለማሳሰብ ነው፡፡የሚቀጥለው ሠንጠረዥ የሚሳየን ታሪካዊውን የክርስቲያን አምልኮ አጭር መግለጫ

ነው፡፡በዚህ ሠንጠረዥ የተገለጠው የትኛወንም ክፍል ቢሆን ለዘመርና በንግግር ሊገለጥ ይችላል፡፡በዚህ ዝርዝር ወስጥ በተይም ለአምልኮ መጥራት ከሚለው ቀጥሎ ተጨማሪ የሚዘመሩ አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ መዝሙሮች ማካተት ይቻላል፡ ወይም ከመባ በኋላ ለማዘጊያ የሚሆን መዝሙር ማካተት ይቻላል፡፡

በዚህ ሠንጠረዥ እንደተገለጠው ዓይነት ያምልኮ ሥርዓት በየትኛወም ቤተክርስቲያን ላይገኝም ይችል ይሆናል፡፡ይሁን እንጂ በሺህ የሚቆጠሩ አብያተክርስቲያናት በዚህ ሠንጠረዥ የተጠቀሰወን ግብዓት ዓይነት ይጠቀማሉ፡፡ያስተወሉ በዚህ ሠንጠረዥ አወቃቀር ወስጥ መሠረታዊ የሚስተዋል ጥበብ ተገልፆአል፡፡የእግዚአብሐር ቃል አንደኛ ነው፡እኛን ወደ አምልኮ ይጋብዘናል እኛም ደግሞ በአድናቆትና በአክብሮት ምላሽ እንሰጣለን፡፡የእግዚአብሐር ቃል ለንሰሀ ይጋብዘናል፤እኛ ደግሞ ለመታደስ በንሰሀ ወደ እግዚአብሐር እንመለሳለን፡፡የእግአብሐር ተስፋ ወደ ምስጋና ይመራናል ሌሎችንም እንደዚሁ ማለት ነው፡፡

ልብ ይበሉ በዚህ ዓይነት የሚለመድ አምልኮ የሁለትዮሽ ግኑኝነት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡አምልኮ በእግዛብሐርና በተሰበሰበው ማህበር መካከል የሚደረግ የንግግር መለዋወጥ ነው፡እግዚአብሐር ይናገራል ጉባኤው ይሰማል፤ጉባኤው ይናገራል እግዚአብሐር ያዳምጣል፡፡ስለዚህ በሰንጠረዡ ላይ የሚታየው ቀስት አምልኮ ከእግዚአብሐር ወደ ሕዝቡ ከሕዝቡ ደግሞ ወደ እግዚአብሐርና በሕዝቡ በእርስ በርስ መካከል የሚደረግ የንግግር መለዋወጥ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ማሰብሰብ | ጉባኤውን ወደ አምልኮ መጥራት ↓<br>ሰላምታ ↓<br>የአክብሮት ወይም የመግቢያ ፀሎት ↑<br>ወደ ንሰሀ መጥራት ↓<br>የንሰሀና የማዘን ፀሎት ↑↔<br>ይቅርታን ማወጅ ↓<br>ሰላምን ማወጅ ↓↔<br>ምስጋና ↑<br>ሕጉ ↓<br>ውሳኔ ማድረግ ↑↔ |
| ማወጅ | ቃሉ እንዲገልጥልን መፀለይ ↑<br>ከቃሉ ማንበብ ↓<br>ስብከት ↓ |
| ለቃሉ ምላሽ መስጠት | የእምነት መግለጫ ↑<br>የጉባኤ ፀሎት ↑ |

| | |
|---|---|
| | መባ ↑ |
| የጌታ እራት | የእግዚአብሔርን ተስፋና ግብዣ ማወጅ ↓<br><br>የምስጋና ፀሎት ↑<br><br>ሕብስቱን መካፈል ↓<br><br>ሕብረት ማድረግ ↑↔<br><br>የምስጋና ምላሽ መስጠት ↑ |
| መላክ | ለደቀመዝሙርነት ወይም ለአገልግሎት ማነሳሳት↓<br><br>ቡራኬ ↓ |

በአጣቃላይ በዚህ የአምልኮ አገልግሎት ማዋቅር የስነ መለኮት ጥበብ ወይም የሚስተዋል ጥበብ አለ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ወስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለእያንዳንዱ የአምልኮ ተግባር አስፈላጊነቱና ትርጉሙ እንዲጎላ ተደርጓል፡፡

እንግዲህ ይህን ሁሉ በሥርዓት ለማሆን አገልግሎት "ከዝርዝር አቀራረብ" ይሻላል የሚል እደምታ አለን፡፡ በዚህ ሁሉ ወስጥ (ምስጋና፣ምልጃ፣የኃይማኖት መግለጫዎች ምስክርነት) የትኛው ከየትኛው መከተል እንዳለበት ሳይገለጽ በደፈናው ተዘርዝረዋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አገልግሎት ወቅት የግል የአምልኮት ተግባር የበለጠ ትርጉም ይሰጥ ይሆናል፡፡ ቢሆንም ወጥ የሆነ አምልኮ ደግሞ የበለጠ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ማዝምራን "አሰደናቂ ፀጋ" የሚለወን መዝሙር ለማዝሙር በዝግጅት ላይ ይሆኑ ይሆናል፡፡ የትም ቢዘመር ሚዜቃው በራሱ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ ነገር ግን እስቲ ለአንድ አፍታ ያስቡ መዝሙሩ ከንሰሀ ፀሎትና ከፀጥታ በኋላ ቢዘመርሳ፡፡ እግህዲህ ይህንኑ መዝሙር በአምልኮ አገልግሎት ወቅት በአወዱና በትክክለኛ ቦታው ሲዘመር የበለጠ ኃይል ያለው መዝሙር ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይህንን ታሪካዊ የአምልኮ ሥርዓት ይዘት የትኛወንም ዓይነት የአሜሪር ዘዴ፣ ሚዜቃ፣ ሥነ ጥበብ ወይም ድራማ በማከል የአምልኮ ሥርዓቱን ማጠቀም እንዳለብን አያስገድደም፡፡ ነገር ግን ይህንኑ አንድ ዓይነት ሥርዓት በሚመስል መልኩ በሃያቲ ሀገር በጎጆ ቤት ወስጥ የሚያመልኩም ይሁኑ ወይም በአወሮፓ አህጉር በትላልቅ ካቴድራሎች ለሚያመልኩ የተወሰነ ለወጥ በማድረግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የትኛወም ማኅቢና የአምልኮ ሜሪ እንደ ግብዓት ሊጠቀምበትና ትልቅ ትምህርት ሊቀስምበት የሚቻል በአለማቀፍ ይዘትነቱ እወቅና ያለው ነው ለማለት ያስችላል፡፡

## መንፈስ ቅዱስ እና አምልኮን የማዘጋጀትና የመምራት ተግባር

በዚህ የአምልኮ ሥርዓት አመለካከት፣የመጽሐፍት ጥቅሶች እና ፀሎዮች ልክ እንደዚህኛው መጽሐፍት ማለት ነው ብዙዎችን ያስጨንቃቸዋል፡፡ በክርስቲያኖቸ አማካኝነት ጥቅም ላይ የዋሉ የፀሎት መጻሕፍት፣ያለዝግጅት የሚፀለይን ፀሎት አያበረታታም የሚል እደምታ ነበረ፤ ይህ አባባል ደግሞ ዛሬም አለ፡፡ እንዲያወም እንደ ሥርዓት ብቻ የሚያገለግል ነው በማለም ይታማል፡፡ በእርግጥ ለእንደዚህ ዓይነት ጥቅም የሚውሉ የመጻሕፍት ጥቅሶች አይረባም ወደ ሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ይችል ይሆናል፡፡

በእርግጥም የአምልኮ መዝ ትርጉሙን ሳይገነዘብና ሳይረዳው ዝምብሎ “ከመጽሐፍ አውጥቶ ቢያነብ” አንዳንድ አማኞች ሊያሳስባቸውና “በንባብ የሚደረግ ፀሎት ሙት ነው” ወደ ሚያስብል ድምዳሜ ሊወስዳቸው ይችል ይሆናል፡፡

እነዚህ ሁሉ ዋጋ የሚሰጣቸው አሳሳቢ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ምክንያቱም አምልኮን ሊያደናቅፉ ይችላሉና ሊቀረፉ ይገባል፡፡ በተለይም አምልኮዋቸው በጽሁፍ በተደገፈ ሚልኩ የሚያካሂዱ ማህበረ ምዕመናን በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት አምልኮዋቸው ደረቅ አምልኮ ነው ሊያስብላቸው ይችላልና፡፡

ነገር ግን የመጨረሻው ታሪክ አሳሳቢው ጉዳይ አይደለም፡፡ በእኩል ደረጃ ደግሞ ችግር ፈጣሪ ሊሆን የሚችለው ማህበረ ምዕመኑ ራሱን ያስገዛበት አወድ ዓይነት ምንነትና ተመጣጣኝ ያልሆነ የጥቂቶች አመራር ተጽዕኖ ነው፡፡ ያለ ዝግጅትም የሚደረግ ፀሎትም ቢሆን ለየት ያለ የመንፈሳዊ አገልግሎት ምላሽ የሚሰጥ መስሎ ቢታይም ቅሉ፤ ከሳምንት ሳምንት ከመጽሐፍት ተወስዶ ከሚነበበው ፀሎት ባነሰ ሚልኩ የተለያየ የፀሎት ዓይነት ሥዕል የሚያካትት መሆኑን ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም ያለፅሁፍ ዝግጅት የሚደረግ ፀሎት አሳሳቢነት ጎልቶ የሚታየው በተለይም ተገቢና እስከ ዛሬ ጥቅም ላይ የሚውለውና የበለፀገ የአምልኮ ሀብት የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሎቶችን ችላ ከማለቱም ሌላ በመዝሙረ ዳዊት የተገለጹት ፀሎቶች ወደማዘንጋት ሊመራ የሚችል ሆኖ ይታያል፡፡

ለአምልኮ የሚጠቅሙ ጽሁፎችና የመሳሰሉት ጥቅም ላይ ማዋል ወይም ለማጠቀም አለመፈለግ ሁለቱም ወደ መፈተን ችግርና ተግዳሮት ወስጥ ሊከቱን ይችላሉ፡፡ ሆኖም እነዚህ ነገሮች በአግባቡ ሊቀረፉ የሚችሉት ቀደም ሲል የተዘረዘሩት ሚልካም ባሕሪያት የአምልኮ መዝው በሥራ ላይ የሚያውል ከሆነ ነው፡፡ ምናልባትም ዋና አሳሳቢ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ልክ እንደዚህ መጽሐፍ የመሳሰሉት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚያዳክሙ ከሆነ ነው፡፡በተለይም በዋንኛነት አሳሳቢ የሚሆነው በጽሁፍ የሚዘጋጁ የአምልኮ መመሪያዎች ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንም ክፈተት ወይም ቦታ የሚይሰጡ ከሆነ ነው፡፡ሁሉም ነገር በጽሁፍ የተደገፈ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ የቱ ጋ ሊሠራ ይቻላል?

ስለዚህ በመጀመሪያ መረዳት ያለብን ነገር ቢኖር ይህ መጽሐፍ ለአምልኮ ዓላማ ማጠቀም ማለት ሁሉንም ነገር በጽሁፍ የተደገፈ ብቻ ይሁን ማለት አለመሆኑን ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ለማለት የተፈለገው ነገር ቢኖር፤ የአምልኮ መዝዎች በተቻለ ማጠን ለመደበኛ አምልኮ አግልግሎትም ይሁን ያለዝግጅት ለሚደረግ መደበኛ ላልሆነ ድንገተኛ አገልገሎት በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት ጠቃሚ ሀሳቦች ሥራ ላይ መዋል እንዲችሉ ማበረታታት ነው፡፡ አብዛኛው የዚህ መጽሐፍ ክፍል የሚያወሳው ሰለጽሁፍ ብቻ ሳይሆን ያለጽሁፍ ዝግጅትም ስለሚደረግም የአምልኮ ሂደት ጭምር ነው፡፡

ይሁን እንጂ በዋንኛነት ሊጠይ የሚገባዉ ነገር ቢኖር ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን አሠራር በተማለከተ ያለንን አማካከት ሚዘም ነው፡፡ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተፃፈዉ የሚሠራ መሆኑን፣በግጥም ሚልክ በተዘጋጀዉ በመዝሙረ ዳዊት እንደሚሠራና ደግሞ በጽሁፍ የተዘጋጀ ነገር ሳይኖር በድንገተኛ አገልግሎት ወቅትም በጴጥሮስና በጳውሎስ እንደሠራ የሚሠራ መሆኑን ይቀበላሉ፡፡

የጥንት ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ በልሳን እንዲናገሩ እንደመራቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ በፍጥረት ወስጥ ለነበረው ማዘበራረቅ ሥርዓትን አበጅቶአል፡፡ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ሥርዓት ባለው ሚልኩም ወይም ያለፅሁፍ ዝግጅት በሚቀርብ አምልኮ መሥራት የሚችል ከሆነ ታዲያ ስለመንፈስ ቅዱስ ያለን ግምት ለምን በጣም ወስን እናደርገዋለን? ለምሣሌ አንዳንዴ “በዚህ ሳምንት የአምልኮ እቅድ ለማውጣት

ጊዜ አልነበረንም ስለዚህ ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ቢሠራን ጫልካም ነው" ወይም እስኪ ዛሬ በዕቅድ ከሚዘጋጅ የአምልኮ ሥርዓታችን ወጣ ብለን መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራ እንተዉለት" ልንል እንችላለን፡፡

*እየተለወጠ ባለ በዚህ ዘመን እውነተኛ አምልኮ* (የክርስቲያን ሪፎርምድ ቤተክርስቲያን ዕትም 1997) ግልፅ ያደረገው ነገር ቢኖር "መንፈስ ቅዱስን ካነሠ ዕቅድ ወይም ካነሠ ሥርዓት ጋር ሚያያዝ የለብንም መንፈስ ቅዱስ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ በሥርዓት በታጀበ አምልኮ በክብር ሊገለጥ ይችላል፡፡ሥርዓት በሌለበትም የአምልኮ አገልግሎት ደግሞ ፈጽሞ ላይገኝ ይችላል፡፡ ከአምልኮ ዓይነትና ሥርዓት ባለፈ ማጠየቅ የሚባው ጥያቄ ቢኖር ይህ የአምልኮ አገልግሎት በኢየሱስ ስም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለእግዚአብሔር ምስጋናን የሚያመጣ ነው ወይ የሚለዉን ነው"(ገጽ 90)፡፡እርግጥ ነው መንፈስ ቅዱስ በጥንቃቄ በተዘጋጀ ሰባኪ *እንደዚሁም ደግሞ* ሰባኪው ባልተዘጋጀበትም ፈገግታ፣ ለመናገር ባላሰበው ከአንደበቱ በሚወጣ አረፍተ ነገርም ሊሠራ ይችላል፡፡ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በንቃት የአምልኮ ዕቅድ በሚያወጡ ኮሚቴዎችም ወይም ያለጽሁፍ ዝግጅት አምልኮ በሚመራውም ሰዉ ፀሎት በሃይል ሊሰራ ይችላል፡፡

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በአምልኮዋችን ላይ በሥራ ላይ መሆንን እንዴት ነው የምንረዳው? ይህ በእኛ ደስታ ወይም ሀዘን ሊለካ አይችልም፡፡ ያለፀሁፍ ዝግጅት አምልኮ ማምራትም ወይም በጽሁፍ ዝግጅት አምልኮ ማምራት የመንፈስ ቅዱስ ማኘት ሊያረጋግጥልን አይችልም፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ የትኛዉንም ሊጠቀም ይችላልና፡፡

ምናልባት አንዱ ጠቋሚ የሚሆነው እኛ ለአምልኮው ያለንን ምላሽ ነው፡፡ እስቲ የሚከተሉትን ከአምልኮ በኋላ የተሰጡ አስተያየቶች ልዩነት አገናዝቡ፡፡ "ዛሬ የሚደንቅ ዝማሬ ነበር " እና "ዛሬ ወደ ጠለቀ ፀሎት ወስጥ እንድገባ የረዱኝን የአምልኮ አገልጋዮችን በጣም አመሰግናለሁ " እንደዚሁም "በጣም ግሩም ስብከት አይደለም?" እና "የዛሬው አገልግሎት የትንሣኤ ጌታ እንድገናኝ ረድቶኛል" አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ዋና ሥራ ሁልጊዜ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ማመልከት ነው፡፡መንፈስ ቅዱስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርና ጠበቃ ነው፡፡ ስለዚህ ከአምልኮ ስንወጣ የዕለቱ የአምልኮ አገልግሎት ያበቃው በሚጽናናትና በክርስቶስ ስላለን ዕምነት በጥብቅ አሳስቦንና ከክርስቶስ ኢየሲስ ጋር አገናኝቶ የለቀቀን እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ስለሠራው ሥራ ደስታ ተሰምቶን ልንወጣ እንችል ይሆናል፡፡

አንዳንድ ዛሬ የምንጠቀምባቸዉ ስለክርስቲያን እምነትና አኗኗር የሚፃገሩ ደህረ አዲስ ኪዳን ጸሁፎች የተዘጋጁት በሮማው ቀሌምጦስ የተፃፉ ናቸው፡፡ ከጸሁፎቹ መካከል የሚከተለዉ ፀሎት ተካቶአል፡፡ " ኦ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት መንፈስ ቅዱስ በልባችን እንዲኖር በሚድረግ በዕምነታችን ሥር እንድንሰድና እንድንተከል እርዳን፤ ገና ያልተረዳነዉንም ግለፅልን የሚያስፈልገንን ደግሞ ሙላብን፤በተረዳነውም የፀናን እንድንሆን እርዳን፤ በአንተ አገልግሎት ደግሞ ያለነቀፉ እንድንሆን እርዳን፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን" ለአምልኮ በምንዘጋጅበት ወቅት እግዚአብሔር አምላካችን ፀጋን በመስጠትና ልክ እንደዚህ የምንናገረዉ ትክክለኛ ቃል በአፋችን በሚድረግ ይባርከን፡፡